3. ስለአማርኛ ስያሜቃላት የተነሱ ችግሮችና መፍትሄዎች

ዶ/ር አንተነህ አራጋው፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ፣ ኢሜል፡ - [anteneharagaw@yahoo.com]

አህጽሮተ ጥናት

ስያሜቃላት *(terms)* በስያሜቃላት ጥናት *(terminology)* የሚጠኑ የአንድ ሙያ ቃላት ወይም የአንድ ሙያ ባለቤት የሆኑ ግለሰቦች የሚገለገሉባቸው ቃላት ናቸው:: ያለስያሜ ቃላት አንድን ልዩ ጽንሰሀሳብ ማመንጨት፣ ሚዳት፣ መሚፈጅ *(retrieve)*፣ ማስተላለፍ፣ መተግበር፣ መተርጎምና መተንተን አይቻልም:: የዚህ ጥናት ዓላማም ስለአማርኛ ስያሜቃላት የተነሱ ችግሮችና መፍትሄዎችን መፈተሽ ነው፡ ፡ በአማርኛ ስያሜቃላት ላይ የተጠኑ ጥናታዊ ጽሁፎች የመረጃምንጮች ሲሆኑ፣ መረጃውን የመሰብሰብ፣ የማደራጀትና የመተንተን ተግባራቱ ዓይነታዊ በሚባለው የጥናት ዘውግ የተመራ ሲሆን፣ ሰነድ ፍተሻም ለመረጃ መሰብሰቢያነት የዋለ ዘዴ ነው፡ ፡ ከአማርኛ ስያሜቃላት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮችምሆነ መፍትሄዎች ከትርጉም፣ ከውሰት፣ ከወጥነትና ከአመለካከት ጋር የተያያዙ ናቸው፡ ፡ የምንጩን ቋንቋ ስያሜ ቃል በትክክል የማይወክሉ ስያሜቃላትን መገልገል አንዱ ችግር ሲሆን፣ በትርጉም ሂደት በታላሚውና በምንጩ ቋንቋ ስያሜቃላት መካከል ሊኖር የሚገባውን ግጥጥሞሽ ማሳደግ ከትርጉም አንጻር ለሚታዩ ችግሮች በዋና መፍትሄነት የተጠቀሰ ጉዳይ ነው፡ ፡ የውሰትን አጠቃቀም አለመረዳት ሁለተኛው ችግር ሲሆን፣ ውሰት የሚጨረሻ የስያሜቃላት ማልሚያ ስልት መሆኑን፣ ውሰት በቃል ብቻ ሳይሆን በጽንሰሃሳብና በቃላት ማበጃ ብልሃቶች በኩል ሊከሰት እንደሚችል መገንዘብ በጽሁፎች የተሰነዘሩ የመፍትሄ ሃሳቦች ናቸው፡ ፡ በጥናቶቹ የተነሳው ሶስተኛው ችግር ከወጥነት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ የውጭ ጽንሰሃሳቦችን ለሚተነትኑ ጽሁፎች መዳዩ ቃላት ማዘጋጀት፣ መዝገበ ስያሜቃላትን ማዘጋጀትና ማሰራጨት እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጅ መዝገበ ስያሜቃላትን ጨምሮ በተለያዩ መስኮች አገልግሎት ላይ የዋሉ መዝገበስያሜቃላትን መመርመርና ዘመኑን እንዲዋጁ ማድረግ በመፍትሄነት የተሰነዘሩ ሃሳቦች ናቸው፡ ፡ በጥናቶቹ የተነሳው አራተኛው ችግር ከይሁንታ ማለትም ከአማለካከት ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ የቋንቋ ፖሊሲ አውጪዎችና ተገልጋዮች ለሀገርኛ ቋንቋዎች ያላቸው ግምት ዝቅተኛ መሆኑ ተመልክቷል፡ ፡ ጥቂት ሊባሉ የማይችሉ ጽሁፎች ግምት ቢሆንም፣ የተገልጋዮች አመለካከት አዎንታዊ መሆኑን ጉዳዩን በተጨበጨከዳሰሱ ጥናቶች ለሚዳት ተችሏል፡ ፡ በአጠቃላይ በአንድ ስያሜቃል ላይ የሚኖር አዎንታዊ ወይምአሉታዊ አመለካከት ምንጩትርጉምወይምውሰት መሆኑን፣ ከአንድ ስያሜቃል ጋር

የተያያዘ የወጥነት ችግር ከትርጉም ጋር ወይም ከውሰት ጋር የሚያያዝ መሆኑን፣ በትርጉምና በውሰት አተገባበር ላይ መስራትም አመላካከትና ወጥነት ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት መሰረታዊ መፍትሄ ነው፡ ፡

ቁልፍ ቃላት፡- ምንጭቋንቋ፣ ስያሜቃላት፣ ተቀባይ/ታላሚቋንቋ

መግቢያ

ስያሜቃላት (terms) በስያሜቃላት ጥናት (terminology) የሚጠኑ በአንድ ሙያ ጥላ ስር ያሉ ግለሰቦች የሚገለገሉባቸው ቃላት ወይም ግላጼዎች (expressions) ናቸው:: የስያሜቃላት ጥናት፣ ስያሜቃላት የሚጠኑባቸውን መርሆአዊና ጽንሰሀሳባዊ መሰረቶች ከማጥናት ወይም ለስያሜቃላት ስነዳ (terminography) የሚውሉ መመሪያዎችን ከማጥናት ወይም የአንድን ሙያ ስያሜቃላት ከማጥናት ጋር ሊያያዝ ይችላል (Cabré 1999፣ 32):: የስያሜቃላት ጥናት የአንድን ሙያ ያሜቃላት ከማጥናት ጋር ሲያያዝ ስያሜቃላቱን በተናጠል ወይም የአንድን ሙያ ስያሜቃላት በሙሉ ከማጥናት ጋር ሊያያዝ ይችላል (Kaguera 2002፣ 32)::

ያለስያሜቃላት አንድን ልዩ ጽንሰሀሳብ (ሳይንሳዊ ውይም ቴክኒካዊ እውቀት ወይም መረጃ) ማምነጨት፣ ሚዳት፣ መሚጅ (retrieve)፣ ማስተላለፍ፣ መተግበር፣ መተርጎምና መተንተን አይቻልም (UNESCO 2005):: ስያሜቃላት ለአንድ ቋንቋ ተግባቦታዊ ብቃትና ህልውና ተጨበጭ ማሳያዎች ናቸው:: ከዚህ አንጻርም የአንድ ቋንቋ መድብለ ቃላት ብዛትና አይነት የቋንቋውን ተገልጋይ ማህበረሰብ ደረጃ ለመለካት እንደተለዋዋጭመጠቀምይቻላል::

በስያሜ ቃላት ጥናት የተሰማሩ ሊቃውንት የተለያዩ ጉዳዮችን የጥናታቸው ማእከል እንደሚያደርጉና ከጉዳዮቻቸው ይዘት አንጻርም አምስት የምልከታ አቅጣጫዎች ማግኘት እንደምንችልና በምልክታዎች መካከልም መስተጋብር ያለ መሆኑን እንደ Antia (2000:38) ያሉ ሊቃውንት የስረዳሉ፡ ፡ በመካከላቸው ያለው መስተጋብርም የስያሜቃላት ምልከታዎችን ስነልሳናዊ፣ ስያሜቃላዊ (ስርአተስያሜቃላዊ)፣ እውቀታዊና ተግባቦታዊ፣ እንዲሁም ይሁንታዊ በሚሉ አራት ምድቦች እንዲመደቡ ያደርጋቸዋል፡ ፡ ስነልሳናዊ ምልከታ የስያሜቃላትን ምንጭ በመመርምር ላይ ያተኮረና ጽንሰሃሳባዊ ትንታኔዎችን የሚጋብዝ ምልከታ ነው፡ ፡ ለዚህም በስዋሂልኛ ስያሜቃላት በፍች ለውጥና በሀረግ ቅንጅት የተገኙትን ስያሜቃላት እንዲገልጹ ከተፈለገውጽንሰሃሳብ ጋር በማነጻጸር በKummer (1983) የተደረገውን ትንተና እና የምንጩ

ቋንቋ ቅጣዮችና ውስብስብ አናባቢዎችን ከማለመድ አንጻር የሚታየውን የወጥነት ችግር በመመርመር በMdee (1983) የተደረገውን ትንተና መጥቀስ ይቻላል (Antia 2000፣ 40)፡ ፡

ስያሜቃላዊ ምልከታ የስያሜቃላት ስብስብ በጽንሰሃሳቦች መካከል ያለውን ግንኙነት ማሳየት መቻሉን የሚመረምር ነው፡፡ ለዚህ ምበ MacWilliam (1985) በስዋሂልኛ ቅድመቅጣዮች እንዲገልጹ ከተፈለገውየጽንሰሃሳብ ስርዓት ጋር በማነጻጸር የተደረገውን ትንተና መጥቀስ ይቻላል (Antia 2000፣ 42)፡ ፡ጥናቱ በስዋሂሊኛና በምንጩቋንቋ ቅድመቅጣዮች መካከል መኖር የሚገባውቅርጻዊ ግጥጥሞሽ በመዛነፉ፣ የጽንሰሃሳብ/የስያሜቃላት ግጥጥሞሹ እንዲዛነፍ ምክንያት መሆኑን አሳይቷል፡ ፡

እውቀታዊና ተግባቦታዊ ምልከታ ስያሜ ቃላቱ በአንድ ሙያ ጥላ ስር ማካተት የሚገባቸውን ጽንሰሀሳቦች በምልአት ማካተት መቻላቸውን በመመርመርላይ ያተኩራል:: እንደ Jernudd & Neustupny (1991፣ 31) በዚህ ዓይነቱ ስያሜቃላት ምልከታምስያሜቃላት በልዩ ልዩ ተግባቦታዊ አውዶች (በአርትኦት፣ በመማር-ማስተማር፣ መማሪያ ጽሁፎችን በማዘጋጀት፣ በስልጠና፣ ቤተሙከራን ጨምሮ ልዩ ልዩ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት) ማ ምም አስፈላጊ እንደሆነ ይሞከራል (Antia 2000፣ 79)፡ ፡ ከዚህ አንጻር በተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች የተደረጉ ጥናቶች የሚያሳዩት ሀገርኛ ቋንቋዎች ችግር ያለባቸውመሆኑንነው፡፡ በስዋሂሊኛየመኪናምህንድስናንበተመለከተ የተሰናዱት ስያሜቃላት በመጠናቸውብቻ ሳይሆን በሽፋናቸውም(የተለያዩ መስኮችን የሚያካልሉ) ውስን መሆናቸውንና ስያሜቃላቱ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ ድርሳናትን ለማዘጋጀት በቂ አለመሆናቸው ተረጋግጧል (Mdee 1981፣ Samson 1991 እና Awobuluyi 1994፤ በAntia 2000፣ 44፤ እንደተጠቀሰው)፡ ፡

አመለካካታዊ ምልከታ የሜጨረሻው ምልከታ ሲሆን ይህምየስያሜቃላትን ተቀባይነት የሚመረምር ነው፡ ፡ ተገልጋዩ ማህበረሰብ በእጩት የቀረቡ ስያሜቃላትን ትክክለኛነት፣ ቅቡልነትና መደበኛነት ደረጃ ለመዳኘት ተግባራዊ ይደረጋል፡ ፡ አንድ የተቀባይ ቋንቋ ስያሜቃል ከየትኛው የምንጭ ቋንቋ ስያሜቃል ጋር የበለጠ ግጥጥሞሽ እንዳለው ለመዳኘትም ይረዳል፡ ፡ ይህን በተመለከተ በሃውሳና በካኑሪ ቋንቋዎች በመገናኛ ብዙሃን ጥቅም ላይ የዋሉ ስያሜቃላትን ተገልጋዩ እንዴት እየተረዳቸው እንደሆነ የመረመረው የAskira (1994) ጥናት፣ በስዋሂልኛ ለተለያዩ መስኮች ለተዘጋጁ ስያሜቃላት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያላቸውን እውቅናና አጠቃቀም የመረመረውየ Kummer (1983) ጥናት ተጠቃሽ ናቸው(Antia 2000፣ 42-43)፡ ፡

በአጠቃላይ ከላይ በአጭሩ የቀረበውጉዳይ ስያሜቃላት ከተለያዩገጾች አንጻር የጥናት ርእሰ ነገር ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚያሳይ ነው፡ ስያሜቃላት ከቋንቋ ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከትርጉምና ከተገልጋዩ ማህበረሰብ ጋር የሚነካኩናቸው፡፡

አማርኛ በኢትዮጵያ ታሪክ በጋራ መግባቢያነትና በሀገረመንግስት ግንባታ ሰፊ ቦታ የሚሰጠው ቋንቋነው፡፡አማርኛ የቤተመንግስት (የህግና የአስተዳደር) ቋንቋ የሆነውከ 13ኛ ውክፍለ ዘመን ጀምሮ ነው፡ ከአክሱምዘመን መንግስት ማሽቆልቆል ጀምሮ እስከዘጉዌ ዘመነ መንግስት መባቻ ድረስ የነበሩ በሌላ ቋንቋ አፍፈት የነበሩ የኢትዮጵያ አጼዎችና ነገስታት አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸውነበር፡፡ ከ14ኛውክፍለዘመን ጀምሮ ደግሞበጽህፈት አገልግሎት ላይ ውሏል (Zelalem 2012፣ 5፤ Rubenson (1987)ን እና Teshome (1997)ን ጠቅሰውእንደገለጹት):: የተለያዩነገስታት (የአጼ ቴዎድሮስ፣ የአጼ ዮሐንስ፣ የአጼ ምኒልክና የሌሎች) ታሪከነገስት ተጽፎ የሚገኘው በአማርኛ ነው (Zelalem 2012፣ 7፤ Meyer (2006)ን ጠቅሰውእንደገለጹት)፡፡ አማርኛዘመናዊ ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ ልሳነ ምድር ከገባበት ማግስት አንስቶ ወደትምህርት ቤት ከገቡ ቀደምት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችም የሚጠቀስ ምነው(Bloor እና Tamirat 1996፣ 326):: ይህ ም አማርኛ ለልዩ ተግባቦት የዋለ ቀደመት ቋንቋ እንዲሆን አስችሎታል::

በአማርኛ ስያሜቃላት ላይ ጥናት ማድረግ የተጀመረው ከ1960ዎቹ አካባቢ ነው፡ ይህ ጉዳይ አሁንምከተለያዩ ጉዳዮች አንጻር የምርምር ርእሰነገር እንደሆነ ነው፡ በመሆኑምበአማርኛ ስያሜ ቃላት የተነሱ ችግሮችንና መፍትሄዎችን መዳሰስ በቋንቋው ስያሜቃላት በአጠቃላይም ትምህርትን ጨምሮ ቋንቋውን በተለያዩ መደበኛ አውዶች ለመጠቀምያሉበትን ችግሮች ለይቶ ጣልቃ ለመግባት አስፈላጊ ግብአት ነው::

የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማበአማርኛ ስያሜቃላት አጠቃቀምየተነሱ ችግሮችና መፍትሄዎችን መቃኘት ሲሆን፣ ይህ ዋና አላማምየሚከተሉትን ዝርዝር አላማዎች መነሻ ያደርጋል:-

(1) በቋንቋውስያሜቃላት የተነሱ ዋና ዋና ችግሮችን መለየት፤

(2) ለችግሮቹ በምንጭነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ጉዳዮችን መመርመርና

(3) ለችግሮቹ የተሰጡየ መፍትሄ ሃሳቦችን መለየት ናቸው፡፡

የ ጥናቱ አስፈላጊነ ት

ጥናቱ ትምህርትን ጨምሮ ወደመደበኛ አገ ልግሎት ከመጡ ሀገ ርኛ ቋንቋዎች ቀደምትና አንዱ በሆነ ው አማርኛ ላይ መካሄዱ የ አማርኛን እ ግር ተከ ትለ ው ወደ ልዩ ልዩ አገ ልግሎቶች ለማጡና ወደፊትም ለሚማጡ ሀገ ርኛ ቋንቋዎች የ ሚኖረው ፋይዳ እ ንደተጠበቀ ሆኖ ለሚከ ተሉት ጉዳዮች አ ስተዋጾ ይኖረዋል ተብሎ ይገ መታል:-

(1) በ ግል ምሆነ በ ተቋምደረ ጃ ሀገ ርኛ ቋን ቋዎችን በ ማል ማት ለ ተሰ ማሩ ተቋ ማትምሆነ ግለ ሰቦች ሊያ ጋ ጥሙየ ሚችሉ ችግሮችን ከነ ምን ጩቹ ውበ ሚሊ ዳት አ ስፈላጊ ውን ዝግጅት ለማድረግ ይረዳቸዋል፤

(2) ሳይንሳዊና ቴክኒ ካዊ ጽሁፎችን በ መጻፍ፣ በ መተርጎ ም፣ በ መተንተን ና በ መመረጅ ተግባ ር ላይ ለተሰ ማሩ አ ካላት አ ሚርኛን ጨምሮ በሀገ ርኛ ቋንቋዎች ስያ ሜቃላት ላይ ሊያ ጋ ጥሙስ ለ ሚችሉ ችግሮች፣ ምን ጮችና መፍትሄ ዎች ግንዛ ቤ እ ን ዲኖራቸውያ ደር ጋ ል፤

(3) በ ሚጨረሻ ምጥና ቱ በአ ማርኛስ ያ ሜቃላት ችግሮችምሆነ መፍትሄዎች ላይ ጥና ት ማካ ሄድ ለ ሚፈልጉ አ ጥኝዎች በ መነ ደርደሪያነ ት ያገ ለግላል፤

የ ጥናቱ ዘዴ

የ ዚህ ጥናት ዋና አ ላማበአ ማርኛ ስያ ሜቃላት አ ጠቃቀምየ ተነ ሱ ችግሮችና መፍትሄ ዎች መቃኘት ነ ው:: ለ ጥናቱ በ ግብአ ትነ ት የ ዋሉ መረጃዎችምስለ አ ማርኛ ስያ ሜቃላት በ ተቋ ምና በ ግለ ሰብ ደረ ጃ በተለ ያዩ ወቅቶች የ ተጠኑ ጥና ታዊ ጽሁፎችና ከቋን ቋው ስያ ሜ ቃላት አ ጠቃቀም ጋር የ ተያ ያዙ ጉ ዳ ዮችን ከ ሚያ ነ ሱ ልዩ ልዩ ጽሁፎች የ ተገ ኙ ና ቸው:: አ ጠቃላ ይ የ ጥና ቱ ሂ ደ ት በ አ ይነ ታዊ ዘዴ (qualitative) የ ተመራ ሲሆን መረጃ የ ማሰባሰቡ፣ የ ማደራጀቱና የ መተን ተኑ ተግባ ር በ ድርሳን ትንተና የ ተከ ናወነ ነ ው::

የ ተነ ሱ ችግሮችና መፍትሄዎች

ከአ ማርኛ ስያ ሜ ቃላት ጋር በተያ ያዘ በጥና ታዊ ጽሁፎች የ ተነ ሱ ችግሮችም ሆነ መፍትሄዎች በ ሚከተሉት 4 (አ ራት) ጭብጦች ላይ ያ ተኮ ሩ መሆናቸውተረ ጋግጧል:-

(1) ከትርጉ ም ጋር የ ተያ ያዙ

(2) ከውሰት ጋር የ ተያ ያዙ

(3) ከወጥነ ት ጋር የ ተያ ያዙ

(4) ከአመለካከት ጋር የተያያዙ

ከዚህ በመቀጠልምእነ ዚህን ቅደምተከተል መሰረት እንመለከታለን፡ ፡

(1) ከትርጉምጋር የተያያዙ ችግሮችና መፍትሄዎች

የምንጩ ቋንቋ ስያሜቃል በትክክል የሚይገልጹ ስያሜቃላትን ማልገል ጥቂት ሊባሉ ለሚይችሉ ጥና ታዊ ጽሁፎች ገፊ ምክ ን ያ ት ሆኖ ተገ ኝ ቷል፡፡ ከ ዚህ አ ን ጻ ር ም የ Hailu (1971)ን፣ የ Amsalu (1987)ን፣ የ Polacek (1987)ን፣ የ አ ምሳ ሉ (1980)ን፣ የ አ ባ ትዬ (1980)ን፣ የ Takkele (2000)ን እና የ Aragaw (2008)ን ጽሁፎች መጥቀ ስ ይቻላ ል :: የ ተር ጓ ሚዎች የ ቋን ቋ እ ውቀ ትና የ ትር ጉ ም ክ ህ ሎት ዝቅተኛ መሆን ደግሞ ለ ተጠቀ ሰ ው ችግር በ ዋና ምንጭነ ት የ ተጠቀ ሰ ጉ ዳይ ነ ው (Takkele 2000):: ይህ ችግር ም ጥቂ ት ያ ል ሆኑ የ ተቀባ ዩ ቋን ቋ ስ ያ ሜቃላ ት ከ ምን ጨቋን ቋ ስ ያ ሜቃላ ት ፍቻዊና አገ ባባዊ ባህሪ እ ን ዲሁም ቅር ጻ ዊና ስ ር ዎቃላ ዊ ባ ህ ሪ ጋር እ ን ዳይጣጠሙያደረ ጋ ቸው መሆኑ ተለ ይቷል (Polacek 1987 እና Takkele 2000)፡ ፡

የ ሚከተሉት ደግሞከትርጉምአንጻር ለሚታዩ ችግሮች እንደመፍትሄ የቀረቡ ሃሳቦች ናቸው፡ ፡

(1) የ ምንጨቋን ቋ ስ ያ ሜቃል የ ሚገልጸ ውባህሪ ውጫዊወይምውስጣዊ መሆኑን መረዳት (Amsalu 1987)፤

(2) በ ታላ ሚውና በ ምንጨቋን ቋ ስ ያ ሜቃላት መካከል ቢያ ን ስ በ ሁለት መንገ ድ ሊገ ለ ጽ የ ሚቻል ግጥጥሞሽ እ ን ዲኖር ማድረ ግ (Hailu 1972) እ ና

(3) በ ትር ጎ ምሂ ደት ለ ቅጥዎቹምዋጋ መስጠት ያ ለ ብን መሆኑን ማገ ን ዘ ብ (አ ምሳሉ 1980) ና ቸው፡ ፡

ከ መጀመሪያ ውየ መፍትሄ ሃ ሳ ብ ጋር በተያ ያ ዘ አ ን ድን ስ ያ ሜቃል ከ ምንጭቋን ቋ ወደ ታላ ሚውቋን ቋ ለ መተርጎ ምሁለ ት ብልሃ ቶችን መጠቀምይቻላ ል፡ ፡ አ ን ደኛ ውብልሀ ት በ ጽን ሰ ሀ ሳ ቡ ውስጣዊ ባ ህ ሪ ላይ የ ተመሰ ረተ ሲሆን ሁለ ተኛ ውብልሀ ት ደግሞ በ ጽን ሰ ሀ ሳ ቡ ውጫዊባ ህ ሪ ላይ የ ተመሰ ረተ ነ ው (Amsalu 1987:18-19):: በ ጽን ሰ ሃ ሳ ቡ ውስ ጣዊ ባ ህ ሪ ላይ የ ተመሰ ረ ተው ብል ሀ ት የ ጽን ሰ ሀ ሳ ቡን ቅር ጽ፣ ይዘ ት፣ ጥን ካሬ ወይምስ ሪት መነ ሻ የ ሚያ ደር ግ ነ ው፤ ለ ዚህ ም„ሀ -ቱቦ“ (= U-tube) ተጠቃሽ ነ ው:: የ ጽን ሰ ሀ ሳ ቡን ውጫዊባ ህ ሪ መነ ሻ ያ ደረ ገ ው ብል ሀ ት ደ ግሞ አ መራረ ቱን ፣ ፈል ሳ ፊውን ወይም አ ምራቹን ና የ ተሰ ራበ ትን ቦታ መነ ሻ ያ ደ ር ጋ ል ፤ ለ ዚህ ም „የ እ ን ስ ሳ ት ውጤት“ (= animal product) ተጠቃሽ ነ ው፡ ፡

ከ ሁለ ተኛ ው የ መፍትሄ ሃ ሳ ብ ጋር በተያ ያ ዘ ደግሞ ስ ር ዎቃላ ዊ ፍች፣ ቅር ጽና ውክ ል ና በ ታላ ሚና በ ምን ጭ ቋ ን ቋ ስ ያ ሜቃላ ት ሚካከል ሊታዩ የ ሚቻሉ ግጥጥሞሾች ሲሆኑ ፣ የ ሁለ ቱ ቋን ቋዎች

ስያሜቃላት ቢያንስ በውክልና መገጣጠም እንዳለባቸው ይመከራል:: ከስያሜ ቃሉ ቅርጽ አንጻር መኖር የሚገባው ግጥጥሞሽም ቅጥያዎች ድረስ መዝለቅ አለበት፡ ፡ የአምሳሉ (1980) ጹሁፍ ለእንግሊዝኛ ቅጥያዎች አቻ ሊሆኑ የሚችሉ የአማርኛ ቅጥያዎችን በማዘርዘር ያሳያል፡ ፡ ይህም በውሰትም ሆነ በሌላ መንገድ ቃላትን ወደተቀባዩ ቋንቋ ለማምጣስ ለሚፈልጉ ተርጓሚዎች የሚኖረውአስተዋጽኦ ቀላል አይደለም፡ ፡

ከላይ ከቀረቡት የመፍትሄ ሃሳቦች በስተጀርባ ከትርጉም አንጻር በአማርኛ ስያሜቃላት ላይ የሚታዩ ችግሮችን ማየት ይቻላል፡ ፡ የምንጩ ቋንቋ ስያሜቃል ስርዎቃላዊ ፍች ብቻ የሚወክል ቃል መጠቀም አንዱ ችግር ነው፡ ይህ ም የተቀባዩን ቋንቋ ስያሜቃልውክልና የዘነጋ ስለሚሆን የጽንሰሃሳብ መዛባትን ያስከትላል፡ ፡ ከምንጬ ቋንቋ ቅርጽ ጋር የማይገጥም ቃል መጠቀምም ሌላው ከትርጉም ጋር ሊያያዝ የሚችል ችግር ነው፡ የቅርጽ አለመገጣጠም ለምንጬ ቋንቋ ቅጥያዎች ጥንቃቄ ካለማድረግ ሊከሰት ይችላል፡ ፡ ይህምየምንጩ ቋንቋ ቅጥያዎች ካለመተርጎም ወይምቅጥያዎቹን ሊተካ በማይችል የተቀባይ ቋንቋ ቅጥያ በመተርጎምየሚከሰት ነው፡

(2) ከውሰት ጋር የተያያዙ ችግሮችና መፍትሄዎች

በአጠቃላይ በጽሁፎቹ በተለያየ መንገድ እንደተገለጸው ከውሰት ጋር የተያያዙ ችግሮች እንደሚከተለውበሶስት መልኩየሚገለጹ ናቸው፡ -

(1) ውሰት እንዴት ሊገለጽ እንደሚቻል አለሚረዳት፣

(2) የምንጩ ቃል እንዳለ መዋስና

(3) ውሰትን የመንጠቀምበትን ሁኔታ አለመረዳት ናቸው፡ ፡

ብዙ ጊዜ ከቋንቋ ረገድ የሚካሄድ ውሰት በግልጽ ከሚታየውከ ቃላዊውውሰት አንጻር ብቻ የሚታይ ከመሆኑምበላይ በዝምድና ቅርብ ከሆነ ቋንቋ በውሰት ለመጣስያሜቃልና ሩቅ ከሆነ ቋንቋ በውሰት ለመጣስያሜቃል የሚኖረን ግንዛቤ የተለያየ ነው፡ ይህ ም ውሰትን በምን ሁኔታ እንደአንድ የስያሜቃል ማልሚያ እየተጠቀምንበት እንደሆነ በሚኖረን አረዳድ ላይ ልዩነት መፍጠሩ አይቀርም፡ ፡ ከምንጭ ቋንቋ አንጻር ውሰት ውስጣዊና ውጫዊ በማለት በሁለት ይመደባል፡፡ ውስጣዊ ውሰት ግእ ዝን ጨምሮከሀገርኛ ቋንቋዎች የሚካሄድን ውሰት የሚማለከት ሲሆን ፣ ውጫዊ ውሰት ደግሞ እንግሊዝኛን ጨምሮ ከሌሎች የውጭቋንቋዎች የሚደረግን ውሰት የሚማለከት ነው (አምሳሉ 1980)፡ ፡ ከዚህም የምንረዳው አማርኛን በማልማት ረገድ ከሀገርኛ ቋንቋዎች የሚደረግን ውሰት እንደውሰት ያለመቁጠር አዝማሚያ ያለ መሆኑን ነው፡

በሌላ በኩል በተለያየ መንገድ የተገለጸ ቢሆንም ውሰት ቃላዊና ጽንሰሃሳባዊ ተብሎ ሊከፈል የሚችል መሆኑን የተነተኑ ጽሁፎች አሉ፡ ፡ በዚህ ረገድ የሚጠቀሰውየ ፍቅሩ (1964) ጽሁፍ ነው ፡ ጽሁፉ በጽንሰሃሳባዊ ውሰት ወደአማርኛ የገቡ ቃላትን የሚተነትንና ግልጽነታቸውንም ከተገልጋዩ ይሁንታ አንጻር የሚቃኝ ነው፡ የተገልጋዮቹ ይሁንታ ላይ በመመርኮ ዝም፣ ጽሁፉ ጽንሰሃሳባዊ ውሰት ተግባቦትን የሚያደናቅፍ በመሆኑ መበረታት የለበትምየሚል ድምዳሜላይ ደርሷል፡ ፡

ውሰት በቃላት ወይም በጽንሰሃሳብ ደረጃ ብቻ ሳይወሰን የስያሜቃላት ማበጃ ብልሃትንና ቅ ጥዮችን በመዋስ ምሊገለጽ ይችላ ል (Polacek 1987 እና Gankin 1988)፡ ፡ ከአማርኛ ስያሜቃላ ት ጥና ት አንጻር ቃላትን ብቻሳይሆን የቃላት ማበጃ ብልሀትን ና ቅጥዮችን መዋስ እንደሚቻል ለመጀመሪያጊዜ ያሳየ ውበ Polacek (1987) ስራ ነው:: የ Gankin (1988) ስራ ደግሞ ውሰት ቃላትን ፣ ቅጥዮችንና የቃላት ማበጃ ብልሀትን ብቻሳይሆን ሀሳብን ብቻለመዋስ እንደሚስችልምአሳይቷል::

ከ ውሰት ጋር በተያያዘ ወሰትን ፣ በተለይም ቃላዊ ውሰትን ፣ ስለ ማለመድ ትን ተና ያ ደ ረ ጉ ጽሁፎችም አሉ፡ ፡ ውሰትን ማላመድ ውስ ቃሉ ከተቀባዩ ቋንቋ ሰዋስዋዊና አገባባዊባህሪ ጋር እንዲስማማማድርግን ይመለከታል (type/typing እና typist የሚሉትን ቃላት እንደቅደምተከተላቸው መተየብ/ትየባ/ተያቢ በማለት በድምጽምበአገባባዊ ባህሪምእንዳላመድናቸውሁሉ)፡ ፡ የ Abrham (1963) ጽሁፍ ውስ ቃላትን ማላመድእንደሚገባ በዋና ርእሰነገርነት ያነሳል፡ ፡

የምንጩ ስያሜቃል እንዳለ የመዋስ ችግር ከውሰት ጋር በተያያዘ የተነሳ ሁለተኛውችግር ነው ፡ ጽሁፎቹ የዚህ ን ችግር መኖር በተለያየ መንገድ አንጸባርቀውታል፡ ፡ ችግሩን ካዩበት አንጻር ጽሁፎቹን ጅምላ ውሰትን በቀጥት ያወገዙና ጅምላ ውሰትን በተዘዋዋሪ ያወገዙ ብለን ልንከፍላቸውእንችላለን፡ ፡ ጅምላ ውሰትን በቀጥታ ካወገዙት ጽሁፎች መካከል የ Abrham (1963) እና የ Abrham (1966) ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ጽሁፎች ናቸው፡ ፡ የመጀመሪያው ከአማርኛ ጠባይ ጋር እንዲላመዱ ያልተደረጉ ውስ ስያሜቃላትን የሚተነትን ሲሆን፣ የሁለተኛው ደግሞ ሳይችግር ጩውብድር እንዲሉ በአማርኛ አቻ ስላላቸውውስ ስያሜቃላት የሚተነትን ጽሁፍ ነው ፡

ጅምላ ውሰትን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚውግዝ አዝማሚያ ያላቸውጽሁፎች ከውሰት በተጨማሪ ሌሎች የስያሜቃላት ማበጃ ብልሃቶችን በመጥቀስና እነዚህንምበምሳሌዎች በማብራራት ላይ ያተኩራሉ፡ ፡ ይህ ም ውሰት ብቸኛ ውአማራጭእንዳል ሆነ በማሳየት ላይ የተንተራሰ የጅምላ ውሰት መቃወሚያ መንገድ ነው፡ ፡ አንዳንዶች ደግሞ ለትርጎም የሚረዱ ጽንሰሃሳቦችን በማብራራትና በምሳሌም በማሳየት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡ ፡ አንድን የውጭ ስያሜቃል ወደተቀባዩ ቋንቋ ለመመለስ

የሚያስፈልጉ ማከፈርቶችን ለክተው ለማብራራት ከሚፈልጉ ጽሁፎች በስተጀርባ የጅምላ ውሰት ምንጩየ ትርጉምክህሎት መጓደል እንደሆነ ይነ ሳል፡ ፡

ከውሰት ጋር በተያያዘ የተነ ሳውሶስተኛው ችግር ውሰትን የመንጠቀምበትን ሁኔ ታ አለመረዳት ነ ው፡ ፡ የውጭጽንሰሃ ሳቦችን ወደሀገ ርኛ ቋን ቋ በማላመድሂደት ውስ ስያሜቃልን መጠቀምተገ ቢ ወይም የ ሚጨረሻ አ ማራጭየ ሚሆንባ ቸው አ ጋ ጣሚዎች አ ሉ፡ ፡ እ ን ደ Amaslu (1987) እና አ ቦ ነ ህ (1994) የ ሚከተሉት ውሰት ተገ ቢ የ ሆነ ባቸውን አ ጋ ጣሚዎች የ ሚወስኑ ና ቸው፡ ፡

(ሀ) በጣምሚያ ዊ (more specialized) የ ሆኑ ስያሜቃላ ትን አ ለሙተር ጎ ምና

(ለ) በውሰት ወደቋን ቋውየ ገ ቡና የ ለሙዱስያሜቃላ ትን አ ለመተርጎ ምየ ሚሉ ና ቸው፡ ፡

ሃ ሳቦቹ አ ን ድን ቋን ቋ በማልማት ሂደት ውሰት ሁልጊዜ የ ሚወገ ዝ አ ለመሆኑን የ ሚገ ልጹ ከመሆና ቸው ባሻገ ር፣ የ አ ማርኛ ን ስ ያ ሜቃላ ት በ ማል ማት ሂ ደ ት ከ ውሰት ጋር በ ተያ ያ ዘ ሁለ ት ችግሮች ያ ሚታዩ መሆኑ ን ነ ው፤ መተር ጎ ምየ ማይገ ባ ቸውን ለ መተር ጎ ም መሞከ ር ና ከ ዚህ በ ስ ተጀር ባ ደግሞያ ላ ግባ ብ መዋስ ና ቸው፡ ፡

በአ ጠቃላይ የ አ ማርኛ ስ ያ ሜ ቃላ ትን በ ማልማት ሂ ደት ከ ውሰት ጋር በ ተያ ያ ዘ የ ሚታዩ ችግሮች የ ውሰትን መገ ለ ጫ ካለመረዳት፣ በገ ፍ ከመዋስና ውሰትን የ ምንጠቀምባቸውን ሁኔ ታዎች ካ ለ መረ ዳ ት የ ሚመነ ጩመሆና ቸውን መረ ዳ ት ይቻላ ል፡ ፡ ውሰ ትን የ ሚጨረሻ አ ማራጭማድረ ግ፣ ውሰ ት በ ቃል ወይም በ ጽን ሰ ሃ ሳ ብ እ ን ዲሁም ከ ውጭ ወይም ከ ሀገ ርኛ ቋን ቋዎች ሊካ ሄ ድ እ ን ደሚችል ማ ን ዘ ብ በ መፍ ትሄ ሃ ሳ ብነ ት ሊጠቀሱ የ ሚቻሉ ና ቸው ፡

(3) ከወጥነ ት ጋር የ ተያ ያ ዙ ችግሮችና መፍትሄዎች

በተለያየ ደረጃና ሁኔ ታ በ ጥና ታዊ ጽሁፎች እ ን ደችግር ከተነ ሱ ጉዳዮች መካከል የ ስያሜቃላ ት አ ጠቃቀም ወጥነ ት አ ለመኖር ነ ው፡ ፡ ወጥነ ትን የ ሚገዳ ደ ሩ መረ ጃዎች መኖራቸውን በ ጽሁፎች በተለ ያ የ መንገ ድ ተተን ትነ ዋል፡ ፡ ይህ ም በሁለ ት መንገ ድ የ ሚገ ለጽ ነ ው፡ ፡ ለ አ ን ድ የ ውጭ ጽን ሰሃ ሳ ብ ከአ ን ድ በ ላ ይ የ አ ማርኛ ስያ ሜቃላ ትን መጠቀም አ ን ዱ ሲሆን ፣ ለተለ ያ ዩ የ ውጭ ጽን ሰሃ ሳ ቦች አ ን ድ የ አ ማርኛ ስ ያ ሜቃልን መጠቀምደግሞሁለ ተኛ ውነ ው፡ ፡

ለእ ነ ዚህ ችግሮች የ ተለ ያ ዩ ጉዳዮች በ ምን ጭነ ት ተጠቅሰ ዋል፡ ፡ እ ን ደአ ባ ትዬ (1980) የ ሚከ ተሉት ወጥነ ትን የ ሚገ ዳደሩ ምን ጮች ና ቸው፡ -

(ሀ) ለስ ያ ሜቃላ ት ምን ጭመሆን ባ ለ በ ት ቋን ቋ አ ለ መስማማት፤

(ለ) አ ስ ቀድሞበነ በ ረ ውስ ያ ሜቃል ቅር ጽ ወይምይዘ ት አ ለ መስ ማማትና

(ሐ) በስያሜቃልና በጽንሰሀሳብ መካከል ባለውግንኙነት አለመስማማት ናቸው፡ ፡

በ(ሀ) የተጠቀሰው የኢወጥነት ምክንያት ከውሰት ጋር የሚዛመድ ሲሆን፣ በ(ለ) እና በ(ሐ) የተጠቀሱት ነጥቦች ደግሞከትርጉምጋር የሚያያዙ ናቸው፡ ፡

በሌላ በኩል አቦነ ህ (1994) ከወጥነትና በአጠቃላይምበአማርኛ ስያሜቃላት ላይ ለሚታዩ ችግሮች 14 (አስራ አራት) ምንጮችን የዘረዘሩ ሲሆን፣ 13ቱ ምንጮች ከትርጉምና ከውሰት ጋር የተያያዙ ናቸው(ቀሪውለነባር ስያሜቃል አለመጋለጥየሚል ስሜትያለውነው)፡ ፡

ኢወጥነትን ለመቀነስ የተለያዩ መፍትሄዎች የተጠቀሱ ሲሆን፣ መፍትሄዎቹን እንሚከተለው በሶስት ነጥቦች ማጠቃለል ይቻላል፡ -

(ሀ) መዝገበ ስያሜቃላትን ማዘጋጀትና ማስራጨት፤

(ለ) የውጭ ጽንሰሃሳቦችን ለሚተነትኑ ጽሁፎች መዳዩ ቃላት (የእንግሊዝኛ አቻዎችን ያካተተ)ማዘጋጀትና

(ሐ) የሳይንስና ቴክኖሎጅ መዝገበስያሜቃላትን ጨምሮአገልግሎት ላይ የዋሉ መዝገስያሜቃላትን መመርመርና ዘመኑን እንዲዋጁ ማድረግ የሚሉትን ያካትታል፡ ፡

(4) ከአማላካከት ጋር የተያያዙ ችግሮችና መፍትሄዎች

በአማርኛ ስያሜቃላት ላይ የሚታየው አራተኛው ችግር ከአመላካከት ጋር የሚያያዝ ነው፡ ችግሩን እንደዋና ጉዳይ የተነተኑ ጽሁፎች ባይኖሩም አብዛኛዎቹ ጽሁፎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድአመለካከትን ወይምይሁንታን ጉዳያቸውአድርገውታል፡ ፡

ከይሁንታ ወይምከአመለካከት ጋር የተያያዙ ችግሮች አንዳንዶቹ ከአጠቃላይ ከምንጭቋንቋ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ አገልግሎት ላይ ከዋሉ ስያሜቃላት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ጥቂት ሊባሉ የማይችሉ ጽሁፎች ከአማርኛ ስያሜቃላት ጋር ለሚታዩችግሮች መሰረታቸውአማርኛን ጨምሮ ለሀገርኛ ቋንቋዎች ያለ ዝቅተኛ አመለካከት መሆኑን ገልጸዋል፡ ፡ አመለካከቱም ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የሚካ ቢሆንም በዋናነት ግን የቋንቋ ፖሊሲ አውጪዎችንና ተገልጋዮችን ይመለከታል (Abrham 1966፣ Hailu 1971፣ Takkele 2000 እና ተስፋዬ 1964)፡ ፡ ግእዝን ጨምሮ ሀገርኛ ቋንቋዎችን ለአማርኛ ስያሜቃላት ምንጭከማድረግ ጋር በተያያዘ በጋዜጦችና በመጽሄቶች ይደረጉ የነበሩ ውይይቶችንና ክርክሮችን የተነተነው የአባትዬ (1980) ጽሁፍም የቋንቋ ባለሞያዎች ከምንጭቋንቋ አንጻር ያላቸው አማላካከት የተለያየ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡

ተስፋዬ (1964) ደግሞ መምህራን በእንግሊዝኛ ከሚያስተምሩ ይልቅ በአማርኛ ቢያስተምሩ እንደሚቀላቸውመግለጻቸውን ነግረውናል::

በሌላ በኩል ፍቅሩ (1964) ተገልጋዮች የቃልበቃል ትርጉም ቃላት ላይ ያላቸውን አመለካከት ለመፈተሽ ጥረት እንዳደረጉና በዚህ መንገድ ጥቅም ላይ የዋሉት ስያሜቃላትም በተገልጋዮች ዘንድ ግርታ የሚፈጥሩ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡ በአቦነህ (1994) ስያሜለተሰጠውየውጮቃል የተሻለ ስያሜ ማስጠት፣ በውሰት ለለመደየውጭቃል ሀገርኛ ስያሜ(የግእዝ ወይም የአማርኛ) ማስጠትና በስያሜ ቃላት አጠቃቀም ከሌሎች ለመለየት የሚደረግ መሽቀዳደም በሚል የተለዩት የኢወጥነት ምንጮች ከዚሁ ከአማካከት ጋር ሊያያዙ የሚችሉ ናቸው:

አመለካከትን የጥናቱ ርእስ አካል ያደረገውና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተግባር ላይ የዋሉ ስያሜቃላትን መነሻ ያደረገው የAragaw (2008) ጥናት ደግሞ የሚከተሉትን መረጃዎች ይነግረናል፡፡ አብዛኛዎቹ መምህራንና ጥቂት የማይባሉ ተማሪዎች አማርኛ የትምህርት ቋንቋ በመሆኑ እንደሚደሰቱ፣ የአማርኛ ስያሜ ቃላት ከእንግሊዝኛው ይልቅ ግልጽ መሆናቸውን እንደመሰከሩ ይጠቅሳል:: በሌላ በኩል ተገልጋዮች በመማሪያ መጻህፍቱ የተካተቱ ግልጽነት የጎደላቸው ጥቂት የማይባሉ ስያሜ ቃላት እንዳሉና ለማስተማርም ሆነ ለወደፊቱ የተማሪዎች ትምህርት የእንግሊዘኛውን ቢጠቀሙእንደሚሻላቸውመግለጻቸውን ጥናቱ ይጠቁማል:: በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የአማርኛ ሰዋስውን በመማር ማስተማር ተግባር ላይ በዋሉ ስያሜቃላት ወጥነትና ይሁንታ ላይ የተሰራው ጥናትም (Aragaw 2013) ከአመለካከት አንጻር የቃኘው ጉዳይ አለ፡፡ ይህም መምህራን ሲጽፉም ሆነ ሲያስተምሩ የምንጩ ቋንቋ ስያሜ ቃላትን ላለማጠቀም ጥረት እንደሚያደርጉ መጥቀሳቸውንና ይህ ፍላጎታቸውምለተለያየ አይነት አጠቃቀም እንደዳረጋቸው ይጠቁማል::

በአጠቃላይ ከአመለካከት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ጉዳያቸው ያደረጉ ጥናቶች ከፊሎቹ ከምንጭ ቋንቋ ጋር የተገናኙ ችግሮቹን ሲያነሱ ከፊሎቹ ደግሞጥቅምላይ ከዋሉ ስያሜቃላት ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን አካተዋል፡፡ ጥቂት ሊባሉ በማይችሉ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅራቢዎች የቋንቋ ፖሊሲ አውጪዎችና ተገልጋዮች ለሀገርኛ ቋንቋዎች ያላቸው ግምት ዝቅተኛ እንደሆነ ቢገመትም፣ የተገልጋዮችን አማካከት በተጨባጭ በዳሰሱ ጥናቶች ግን የተገልጋዮች አማካከት አዎንታዊ ነው፡፡

ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት በአማርኛ ስያሜቃላት የሚታዩ ችግሮች ከትርጉም፣ ከውሰት፣ ከወጥነትና ከአመለካከት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡ ከትርጉም ጋር የተያያዘው ችግር ከምንጩና ከተቀባይ ቋንቋ እውቀትና እንዲሁም ከሙታረጎሚው ጽንሰሃሳብ እውቀት ጋር የተቆራኘ ሲሆን ከውሰት ጋር የተያያዘው ችግር ደግሞ ውሰትን እንዴትና መቼ የሚለውን መረዳት ጋር የሚገናኝ ነው፡ በሌላ በኩል ከወጥነት ጋር የተያያዙ ችግሮች በቋንቋው የስያሜቃላት አጠቃቀም አንድ ለአንድ ካለመሆኑ ጋር የሚያያዙ ሲሆን፣ እነዚህ ምበዋናነት ከትርጉምና ከውሰት ጋር ከተያያዙ ችግሮች የሚመነጨመሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

አማላካከት የወሰኞችን (የቋንቋና የትምህርት ፖሊሲ አውጪዎች)ና የተገልጋዮችን ይሁንታ የሚማለከት ሲሆን፣ ይኸውም ከምንጭ ቋንቋና ጥቅም ላይ በዋሉ ስያሜቃላት ተገቢነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

መደምደሚያ

ስለአማርኛ ስያሜቃላት ችግሮች ከተነሱ ችግሮችና መፍትሄዎች መረዳት የምንችለውትርጉምላይና በውሰት አጠቃቀምላይ የምንሰራውስራ ወጥነት ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡ ትርጉም ላይ፣ ውሰት ላይና በአጠቃላይም ወጥነት ላይ የምንሰራው ስራም አመለካከት ላይ ተጽእኖ ያደርጋል፡፡ በአንድ ስያሜቃል ላይ የሚኖር አዎንታዊ ወይምአሉታዊ አመለካከት ምንጩትርጉም ወይምውሰት ነው፡ በተመሳሳይ ከአንድ ስያሜቃል ጋር የተያያዘ የወጥነት ችግር ከትርጉ ምጋር ወይምከውሰት ጋር ሊያያዝ ይችላል፡፡ በአጠቃላይ ከትርጉ ምወይምከውሰት ጋር የተያያዘ ችግር ወጥነትና አመለካከት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

አስተያየት

(1) የትምህርት ተቋማት ለሚያሰለጥኗቸውተማሪዎቻቸውብቻ ሳይሆን መገናኛ ብዙሃንን ጨምሮ ቋንቋውን በተለያዩ መደበኛ አውዶች ለሚጠቀሙባለሙያዎች አጫጭር የትርጉም ስልጠናዎችን እንዲያዘጋጁና እንዲሰጡማድረግ፤

(2) ልሳነ ክልኤ የስያሜቃላት መዘርዝሮችንና ልሳነ ክልኤ መዝገበስያሜቃላትን በማዘጋጀት ለተገልጋዩ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፤

የ ዋቢ ጽሁፎች ዝርዝር

ተስ ፋዬ መንገ ሻ :: (1964):: በ ዘ መናዊ ትምህ ር ት ውስ ጥ የ ገ ቡ አ ዳ ዲስ የ አ ማርኛ ቃላ ት:: ለ ትምህ ር ት ባ ችለ ር ዲግሪ ማሟያ የ ቀረ በ ጥና ታዊ ጽሀ ፍ:: አ ዲስ አ በ ባ ፤ ኃ ይለ ስ ላ ሴ ዩ ኒ ቨ ር ሲቲ::

አ ምሳ ሉ አ ክ ሊሉ:: (1980):: የ ውጭቋን ቋ ጽን ሰ ሀ ሳ ብ ትር ጉ ም በ አ ማርኛ፣ in Taddese Beyene and Taddese Tamirat ed., *Journal of Ethiopian Studies,* Vol. XIV (1976-1979). Addis Abbaba: Addis Ababa University.

አ ባ ትዬ አ ን ዳይላ ሉ (1980) የ አ ማርኛ ቋን ቋ ስ ያ ሜቃላ ት በ ድህ ረ አ ብዮት:: ለ ትምህ ር ት ባ ችለ ር ዲግሪ ማሟያ የ ቀረ በ ጥና ታዊ ጽሀ ፍ:: አ ዲስ አ በ ባ ፤ አ ዲስ አ በ ባ ዩ ኒ ቨ ር ሲቲ::

አ በ ነ ህ አ ሻግሬ፡ ፡ (1994)፡ ፡ የ ሙያ ቃላ ት ስ ያ ሜ አ ሳ ሳ ቢነ ት በ ትያ ትር ዘ ር ፍ:: የ ቋን ቋዎች ጥና ት ተቋም *13*ኛው አ መታዊ ጉ ባ ኤ (ገ ጽ 28-34):: አ ዲስ አ በ ባ ዩ ኒ ቨ ር ሲቲ፤ የ ቋን ቋዎች ጥና ት ተቋም::

ፍቅሩ ኪዳነ ማር ያ ም፡ ፡ (1964)፡ ፡ ከ እ ን ግሊዝኛ የ መጣ የ ቃል በ ቃል ትር ጉ ም በ ዘ መና ዊ የ አ ማር ኛ ድር ሰ ት:: ለ ትምህ ር ት ባ ችለ ር ዲግሪ ማሟያ የ ቀረ በ ጥና ታዊ ጽሀ ፍ:: አ ዲስ አ በ ባ ፤ ኃ ይለ ስ ላ ሴ ዩ ኒ ቨ ር ሲቲ::

Abrham Demoz. (1963). European Loan words in Amharic daily News papers. In John Spencer (ed.), *Language in Africa*. Combredge: Cambredge University Press.

_______. (1966). Amharic for Modern Usage (Unpublished).

Amsallu Aklilu. (1987). The Linguistic Theory and Methodology of the Science and Technology Terms Translation Project. In Ermias and Demissew ed., *Proceedings of the International Seminar on Terminology,* June 16-18. Addis Ababa: Ethiopia.

Antia, B.E. (2000). *Terminology and Language Planning: An Alternative Framework of Practice and Discourse.* Amsterdam: John Benjamins PLC.

Aragaw Anteneh. (2008). Terminology Formulation and Usage in Amharic: a Textbook Analysis and a Survey of Primary Schools, MA Thesis; Addis Ababa University Department of Linguistics and Philology, Addis Ababa.

______. (2013). Meta-language Standardization in Amharic. In the *Proceedings of the 4th Annual National Research Symposeum*. June 8-9/2013, Debre-Markos University; Debre-Markos, Ethiopia.

Bloor, T. and Tamrat, W. (1996). Issues in Ethiopian Language Policy and Education. In *the Journal of Multilingual and Multicultural Development*, Vol. 17, No. 5.

Cabré, M. T. (1999). *Terminology: Theory, Methods and Applications*. Amsterdam: John Benjamins

Gankin, E. (1988). Vocabulary Replacement in the Amharic Language and Topical Problems of the Amharic-Russian Lexicography. In *Proceedings of the Ninth International Congress of Ethiopian Studies*. Moscow: Navka Publishers.

Hailu Fulas. (1971). Problems in Terminology. In W. Whitley ed., *Language Usage and Social Change*. London: Oxford University Press.

Kagura, P. (2002). The Dynamics of Terminology. *A descriptive theory of term formation and terminological Growth*,Viii.

Polacek, Z. (1987). Some Theoretical Quuestions of Political and Social Terminology in Amharic. In Ermias and Demissew ed., *Proceedings of the International Seminar on Terminology,* June 16-18, 1986. Addis Ababa: Ethiopia.

Takkele Taddese. (2000). *Ways and Principles of Developing New Words and Technical Vocabulary: The Case of Amharic.* Addis Ababa: AAU Printing Press.

UNESCO. (2005). *Guidelines for Terminology Policies: Formulating and Implementing Terminology Policy in Language Communities.* Paris: Infoterm.

Zelalem Leyew. (2012). The Ethiopian Language Policy: A Historical and Typological Overview. In *Ethiopian Journal of Languages and Literature*, Vol. XII No. 2 June 2012.